MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Department of Facilities Management
DIVISION OF SUSTAINABILITY AND COMPLIANCE

## MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
## ANNUAL NOTIFICATION OF ASBESTOS MANAGEMENT PLAN AVAILABILITY አመታዊ የአስቤስቶስ
## 2025-2026 የትምህርት ዓመት

በ1987፣ የከባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ (Environmental Protection Agency, EPA) ስለ አስቤስቶስ አደገኛነት የፈጣን እርምጃ ህጎችን አፅድቋል-Asbestos Hazard Emergency Response Act (AHERA), 40 CFR Part 763 ። አስቤስቶስ ማቴሪያሎች-asbestos containing materials (ACM) ያሏቸው ፋሲሊቲዎችን በሚመለከት የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች ስለ አስቤስቶስ ማኔጅመንት እቅዶችን እንዲያዘጋጁ ይህ ደንብ ይደነግጋል። የአስቤስቶስ ማኔጅመንት እቅድ የሚከተሉት ይዘቶች ሊኖሩት ይገባል፡-

- ሠርተፊኬት ባላቸው ተቆጣጣሪ ባለሙያዎች አማካይነት በፋሲሊቲው የ ACM ቁጥጥር እና ፍተሻ ውጤቶች፡-
- ህንፃው ያለውን የ ACM አያያዝ ሰፊ እቅድና ማስወገድ የሚቻል ከሆነ የጊዜ ሰሌዳ፣
- የተለመደ የጥገናና የቅነሳ አገልግሎቶች እንደ አስፈላጊነቱ በሚከናወኑበት ወቅት ድንገተኛ የ ACM መፈረካከስን ለማስወገድ የአፈጻጸምና የጥገና መርሃ ግብር፣
- ስለ ACM በተወሰነ ጊዜ የሚካሄድ ፍተሻ እና ያልታሰቡ ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ መወሰድ ያለባቸው የአስቸኳይ እርምጃዎች እቅድ፣ እና
- ሁለገብ የሆነ የአስቤስቶስ መቆጣጠሪያ መርሃ ግብርን በማዕከላዊነት የማቀነባበሪያ መስፈርቶች።

ይህ ማስታወቂያ የተሰጠው የ AHERA ህዝባዊ ማስታወቂያ መስፈርትን ለማሟላት ነው። የእርስዎ ትምህርት ቤት የአስቤስቶስ ማኔጅመንት እቅድ እና በቅርብ ጊዜ የተደረገ የአስቤስቶስ ፍተሻ/ቁጥጥር ሪፖርት እንዲመለከቱት በዋናው ጽ/ቤት ይገኛል።

ከ EPA እና ከሜሪላንድ ስቴት የከባቢ ጥበቃ ዲፓርትመንት-Maryland State Department of the Environment በተገለጸው መሠረት፣ በህንፃዎች ላይ ACM በመገኘቱ ምክንያት ብቻ ለጤንነት የሚያሰጋ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ንጥረ ነገሩ ወይም ማቴሪያሉ ካልተፈረካከሰ ለሰራተኞችም ሆነ ለሌሎች ነዋሪዎች አደጋ አይሆንም። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የአስቤስቶስ ማኔጅመንት ፕሮግራም- የተነደፈው፣ ህንፃው እስከሚወገድ ወይም ከፍተኛ እድሳት ወይም የማስፋፊያ ፕሮጀክት እስከሚካሄድ ድረስ ACM በጥሩ ሁኔታ መያዙን ለማረጋገጥ ነው።

ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎ በዚህ አድራሻ ይከታተሉ፡- Mr. Derek Kwon, Environmental Health Specialist, Environmental Services/Indoor Air Quality Unit, Division of Maintenance, at 240-740-2331 or Derek_H_Kwon@mcpsmd.org.